“እግዚአብሔር፡የመረጣቸውን፡ማን፡ይከሳቸዋል?”

ሮሜ፡ምዕ፡8፤23

## <u>አማላጅነት</u>

የበልዓም፡አህያ፡ዳግም፡ተናገሪ፤

መልዐኩ፡እንዳቆመሽ፡እባክሽ፡መስከሪ፤

ካንቺ፡ያነሱ፡አሉና፡ጭራሽ፡የሚገርሙ፤

የመልዐኩን፡ቃል፡ከቶ፡የማይሰሙ፤

እንደ፡ጌታሽ፡በልዓም፡ከፍተው፡የጠመሙ።

እግዚአብሔር፡በእሥራኤላውያን፡አፍሮ፤

መስዋዕታቸውን፡ተፀይፎ፤

ባዕድ፡አምልኮነታቸውን፡ነቅፎ፤

ቢነሳ፡ሊያጠፋቸው፤

ነቢዩ፡ሙሴ፡ቀረቦ፤

ኃጢአታቸውን፡ይቅር፡ካላልክ፤

በምህረትህም፡ካልተመለስክ፤

እኔን፡ከሕይወት፡መፅሐፍ፤

ደምስሰኝ፡ሰሜ፡አይፃፍ፤

ብሎ፡እኮ፡መናገሩ፤

ሲያማልድ፡ነው፡ምስጢሩ።

ዳዊት፡በመዝሙሩ፡እየተቀኘ፤

ወደ፡እግዚአብሔር፡ለመሄድ፡እየተመኘ፤

በገናውን፡ሲደረድር፡በተመስጦ፤

ስለመልዐኩ፡ሲናገር፡አስረግጦ፤

እንደሚታደግ፡አውቆ፡ጠንቅቆ፤

በሚሰፍሩት፡ሰዎች፡ዙሪያ፡ይሰፍራል፡አለ፤

በመንገድ፡ሁሉ፡ሊጠብቃቸው፤

እቅፍ፡ድግፍ፡አድርጎ፡ሊያነሳቸው፤

ከመጣው፡መቅሰፍት፡ሊያድናቸው።

ሎጥን፡ከሰዶምና፡ገሞራ፤

ማነው፡ያወጣው፡ከነቤተሰቡ፡እየመራ፤

መንገዱን፡ያሳዩት፡ዞዓር፡እንዲገባ፤

መላዕክት፡አይደሉም፡መፅሐፉ፡ይነበባ፤

ምነው፡የዘመኑ፡ሰው፡ግራ፡እንዲህ፡ተጋባ፤

ዓይነ-ሥውር፡ለመሆን፡በራሱ፡እያደባ።

ኢየሩሳሌምንና፡የይሁዳን፡ከተሞች፤

ሰባ፡ዓመት፡ሙሉ፡ቢቆጣቸው፤

ወደ፡አምላኩ፡ቀርቦ፡በትህትና፤

ለሰዎች፡ምህረትን፡ሲማፀን፡በልመና፤

ነቢዩ፡ዘካርያስ፡ሰምቷል፡በጥሞና፤

አምላክ፡ያለውን፡ለመልዐኩ፤

በሚያፅናና፤ቃል፡እንደተመለሰ፡በምህረቱ።

በሚጣፍጠው፡አንደብቱ፤

እንደሌለው፡የሰው፡ብርቱ፤

ሲመሰክር፡ሲያመሰጥር፤

ስሙን፡ጠርቶ፡ሚካኤል፡አለ፤

ይኸው፡ነቢዩ፡ዳንኤል፡ተናገረ፤

ስለ፡ህዝብ፡ልጆች፡እንደሚቆም፡አስተማረ።

ከካህኑ፡ዘካርያስ፡አትማሩም፤

መፃሕፍትንስ፡አትመረምሩም፤

በእግዚአብሔር፡ፊት፡የምቆመው፤

ገብርኤል፡ነኝ፡ሲልስ፡አትሰሙም፤

ምነው፡ዲዳነት፡አማራችሁ፤

እራሳችሁን፡አኮራችሁ፤

አምላክ፡ያለውንስ፡ዘነጋችሁ፤

መልዐኬ፡በፊትህ፡ይሄዳል፤

በፊቱ፡ተጠንቀቁ፤

ስሜም፡በእርሱ፡ነው፡ይላል፤

ይኸው፡ሙሴ፡ምስክር፡ሆኗል፤
ቃሉን፡ጠብቆ፡ባህርን፡ተሻገሯል።
ማማለድ፡እኮ፡ማስታረቅ፡ነው፤
መቼ፡ነው፡ለዓለም፡ድብቅ፡የሆነው፤
አብርሃም፡አይደለም፡የጀመረው፤
ለአምላኩ፡ምርጥ፡ሆኖ፡ያነጋገርው፤
ስለሰው፡ልጆች፡የተማፀነው፤
ፊቱን፡እንዲመልስ፡እባክህ፡ያለው።
ኢዮብ፡ለወዳጆቹ፡ሲፀልይ፡በርትቶ፤
አምላክ፡መቼ፡ዝም፡አለው፡ሁሉን፡ነገር፡ረስቶ፤
በእውነት፡ተቀበለው፡በበረከት፡ሞልቶ።
ዶኪማስ፡ሆይ፡ተነስ፡መስክር፤
ማነው፡የረዳህ፡ልጅህን፡ስትድር፤
ወይኑ፡አልቆብህ፡እንዳታፍር፤
ሰሚን፡ጠርተህ፡ዳግም፡አክብር፤
ዓለም፡ጠፍቷል፡በጥርጥር።

ከኃይለመስቀል፡ተስፋዬ

ለንደን